## ኑ እንተባበር፤ ወቅቱ የሚጠይቀውን የትግል ስልት እንምረጥ፤ ሀገራችንንም ከጥፋት እንታደጋት

### መግቢያ

የዚህ ጽሑፍ አቢይ ዓላማ ሀገራችን ያለችበትን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ ማሳየትና ሀገራችንን አሁን ካለችበት አስከፌ ችግርና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ እየመጣ ካለው አስፈሪ የፖለቲካ ድባብ ለማውጣት ሊኖረን ስለሚገባው ትብብር እና ልንከተል ስለሚገባው  የትግል አይነት የበኩሌን ለመጠቆም ነው።

በጽሑፉ የመጀመሪያ ክፍል እኔን በሚመለከት በብዙዎቻችሁ አእምሮ ውስጥ ሊጉላሉ ይችላሉ ብዬ በማስባቸው ጥያቄዎች ላይ አጭር ማብራሪያ እሰጣለሁ። ከዚያም አሁን በሀገራችን ውስጥ ያለው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ በእኔ እይታ ምን እንደሚመስል የማቀርብበት ይሆናል። በመጨረሻም ሀገራችንን አሁን ካለችበት አስከፌ ችግርና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ እየመጣ ካለው አስፈሪ ሁኔታ ለማውጣት ሊኖረን ስለሚገባው ትብብር እና ልንከተል ስለሚገባው  የትግል አይነት በአጭሩ ጠቁሜ ንግግሬን አቆማለሁ።

በመጀመሪያ በብዙዎቻችሁ አእምሮ እኔን በሚመለከት ብዙ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ ብዬ አስባለሁ። ለምሳሌ የአቋም ለውጥ አድርገሃል ወይ? ከመቼ ጀምሮ ነው የአቋም ለውጥ ያደረከው? አስቀድመህ የአቋም ለውጥ አድርገህ ከሆነ በአንድነት ፓርቲ ምስረታ ሂደት ውስጥ ለምን ተሳተፍክ? ለምንስ ከፓርቲው ወጣህ? የሚሉና ሌሎች በርካታ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። እነዚህ ጥያቄዎች መነሳታቸው አግባብ ነው ብዬ ስለማስብ በመጀመሪያ በእነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ የተወሰነ ማብራሪያ ሰጥቼ ለማለፍ እሞክራለሁ። ሆኖም ምንም እንኳን እነዚህን ጥያቄዎች በሚመለከት ሰፊ ማብራሪያ መስጠት የሚያስፈልግ ቢሆንም የዚህ ጽሁፍ ዋና ዓላማ ስላልሆነ የምሰጠው ማብራሪያ በአጭሩ መሆኑን እንድትገነዘቡልኝ አደራ እላለሁ።

የአቋም ለውጥ አድርገሃል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መጀመሪያ አቋም ከምን? ወደ ምን? የሚለው ነገር በትክክል መታወቅ ይኖርበታል። ቅንጅት ይከተላቸው የነበሩት መሰረታዊ እምነቶቹ ዛሬም እኔም የማምንባቸው እምነቶቹ ናቸው። ቅንጅት እምነቶቹን ለማራመድ የተከተለው ሰላማዊ የትግል ስልት ነበር። ከዚህም አንጻር ሰላማዊ የትግል ስልት መከተል ትክክል ነው ብዬ አምናለሁ። ነገር ግን እኔም ሆንኩ ሌሎች የቅንጅት አመራሮች ሰላማዊ የምንለውን ወያኔ አመጽ/ሀይል እያለው እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል። በመሰረቱ

ሰላማዊ የትግል ስልት በኢትዮጵያ ማድረግ አይቻልም እያሉ ያሉት አቶ መለስ እንጂ ሌሎቻችን አይደለንም። ስለዚህ የአቋም ለውጥ ጥያቄ አቶ መለስ ሰላማዊ ከሚሉት ከሆነ ቀደሞም አቋሜ የተለየ ስለነበር ያደረኩት የአቋም ለውጥ የለም። የበለጠ ለማብራራት ሰላማዊ የትግል ስልት ሲባል በውስጡ የያዛቸው በርካታ ተግባራት/ ድርጊቶች አሉ። ለምሳሌ ቤት ውስጥ መቀመጥ፡ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ፤ የኢኮኖሚ ትብብር መንፈግ፤ ማህበራዊ ማግለል፤ እና ሌሎች በርካታ ድርጊቶች መርዘር ይቻላል። ነገር ግን አቶ መለስና ቡድናቸው ማህበራዊ ማግለልን የዘር ማጥፋት ሙከራ ሲሉት ሌሎቹን ደግሞ አመጽ ይሏቸዋል። እነዚህን ከላይ የዘረዘርናቸውንና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶች ቅንጅት ያስቀመጣቸው ስምንት የዴሞክራሲ ሰርዓት ግንባታ ተቋማት መቋቋም ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኙ ተብሎ የሚደረጉ ከሆነ ደግሞ አቶ መለስ ድርጊቶቹን "አመጽ/ሀይል" አላማውን ደግሞ "ህገ መንግስታዊውን ስርዓት በሀይል የመናድ ሙከራ" ይሉታል። እነዚህንም ፈጽሞ መገኘት በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል ይሆናል ማለት ነው።

ስለዚህ ሰላማዊ ትግል በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል ስለሆነ ማድረግ አትችሉም ከተባልን የተፈቀደልን ህጋዊ ትግል በአጭሩ የትኛው እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን። 1)

የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትንና ደጋፊወችን እያሳደደ የሚያስረውንና ከገዥው ፓርቲ አባላት ጋር ሆኖ የምርጫ ኮሮጆ በጠራራ ጸሃይ የሚሰርቀውን የፓሊስ ተቋም ገለልተኛ ነው ብሎ መቀበል። 2) ኮሮጆ የሚያሰርቀውን የምርጫ ቦርድ ተብዬ ደግሞ በመሰረቱ ገለልተኛ የሆነ ግን የአቅም ችግር ያለበት ተቋም ብሎ መቀበል። 3) የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በመሆናችን ብቻ ደህንነታችንን ስጋት ውስጥ የሚጥለውን ተቋም፡ 4) ሌተቀን በውሸት መአት የሚየደነቁረንን መገናኛ ብዙሃንና 5) የፍትህ ያለህ ተብሎ አቤት ለማለት በሚኬድበት ጊዜ የተከሰስንበትን ድርጊት መፈጸም አለመፈጸማችንን ሳይሆን በአቋማችን ተቃዋሚዎች መሆን አለመሆናችንን ማወቅ ለፍርድ አሰጣጥ ይጠቅመናል በሚሉ ዳኞች ሞልቶ የፍትህ ስርዓቱን የግፈኞች ዋሻ ያደረገውን ተቋም ገለልተኛ ነው ብሎ መኖር ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ነው ይለናል።

ስለዚህ ሀሰትን እውነት፡ ግፍን ፍትህ፤አፈናን ነጻነት፤ጭቆናን ዴሞክራሲ ችጋርን ብልጥግና ኋላ ቀርነትን እድገት ነው ብለህ ኑር ስባል የትክክለኝነት ሚዛን እንደተዛባ ህሊናዬ እያወቀ ለመኖር ስል ብቻ ከምቀበልና የእውነትን ሚዛን ያዛባውን ሀይል ከወያኔ እጅ ለማስጣል ከሚደረግ ማንኛውም ትግል (ወያኔ ምንም አይነት ስም ቢሰጠው) ምረጥ ብባል የኋለኛውን እመርጣለሁ። ምርጫዬም በሞራል መለኪያ ትክክል ነው ብዬ

አምናለሁ። በቅንጅትም ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ወያኔ እንዲህ እያለ እንደሆነ በርግጠኝት ከተረዳሁበት ጊዜ አንስቶ አቋሜ ይኸው ነው። ከዚህ የሚለይ አቋምም ሊኖረኝ አይችልም። ስለዚህ ሰላማዊውን አመጽ፣ ሀሰትን እውነት ነው በል ስባል ትናንትናም ዛሬም ነገም መልሴ አንድ ነው። እምቢኝ። አቋሜም ያው ነው። በመሆኔም ያደረኩት የአቋም ለውጥ ሳይሆን ስለ አቶ መለስና ስለ ቡድናቸው የነበረኝ አመለካከት በጣም ተቀይሯል። ትንሽ ዘግይተሃል ለሚሉኝ ግን ትክክል ናችሁ ከማለት በቀር ሌላ መልስ የለኝም።

ስለዚህ የአቋም ለውጥ አለማድረጌ ከታወቀልኝ ስለ አቶ መለስና ስለሚመሩት ድርጅታቸው የነበረኝ አመለካከት ከመቼ ጀምሮ እንደተለወጠ ልናገር። ወያኔ ወደምርጫ ሲገባ የተሳሳተ ስሌት እንደ ነበረው ሁሉ እኔም ስለወያኔ የተሳሳተ ግምት ነበረኝ። ወያኔ በምርጫው ሊሸነፍ እንደሚችል አስቦ ቢሆን ኖሮ ምርጫው በግንቦት 97 የታየው አይነት ሊሆን አይችልም ነበር። ከምርጫው በኋላ የተከሰቱትም ችግሮች ምናልባት ላይከሰቱ ይችሉ ነበር። በተለይ ከምርጫው በኋላ ቅንጅት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መግንባት የሚያስፈልጉ ተቋማትን በሚመለከት ላቀረባቸውና የወያኔም ህገ መንግስት ለሚደግፋቸው ጥያቄዎች ወያኔ የሰጠው ምላሽ ምን እንደሆነ በሚገባ ሳጤን ከዚያ ሁሉ ውግዘት በኋላ ከእስር ለመፈታት

ያንን ጥያቄ ባቀረበበት ወቅት ነበር ስለ ወያኔ የነበረኝ አመለካከት ሙሉ በሙሉ የተለወጠው።

ጉዳዩ የሀይል ነው። "ሀይል አለኝ ከፈለክ የማቀርብልህን አማራጭ ተቀብለህ መኖር ትችላለህ። ካልፈለክ ቃሊቲ ትበሰብሳለህ" ሲለኝ የነበረኝን አማራጭ ሁሉ ማሰላሰል ጀመርኩ። "ፈርመን እንውጣ ወይስ ይቅርብን" በሚለው ጉዳይ ላይ ስንመካከር ያኔ የነበሩት እንደሚያስታውሱት የእውነትን ሚዛን ያዛባውን ሀይል ከወያኔ እጅ ለማስጣል ምንም አይነት አማራጭ ለመውሰድ የተሻለ እድል የሚሰጠን ፈርሞ መውጣት ወይስ ቃሊቲ መክረም ከሚል አንጻር ልናይ ይገባል የሚል መከራረሪያ ይዤ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ለእኔ የእውነት ሚዛን ህሊናዬ እንጂ ወያኔና የወያኔ ህግጋት አልነበሩም። ዛሬም አይደለም። በዚያ አስጸያፊ ወረቀት ላይ ፊርማዬን ሳኖር ከኛ መካከል አንዳንዶች እንደሚሉት "የወንድ ልጅ በር" አልያም "የማርያም መንገድ" ለወያኔ ልስጠው ብዬ አልነበረም። ድርጊቶቼም ሊመዘኑ የሚገባው ከተዛባ የእውነት ሚዛን አንጻር አይደለም። ሀሰትን እውነት እንድንልና ከህሊና የተጣላን ከዚህም የተነሳ ከፈጣሪ ጋር ከሚያመሳስለን መለኮታዊ ስብእናችን የሚያርቀንን የክፋት ሀይል በምንም አይነት መንገድ ታግለን ማሸነፍ (የምንታገለው ሀይል ለትግላችን

ምንም አይነት ስም ቢሰጠው) በሞራል ሚዛን ትክክል ነው ብዬ አመንኩ።

ወያኔ የከለከለው ስለማይጠቅመው እንጂ ትክክል ስላልሆነ እንደሆነ ከተገነዘብን፤ ወያኔ በፈቀደውና ህጋዊ ባለው ላይ ያልፈቀደውንና ሰላማዊም አይደለም ያለውን ማከል ችግር የለበትም። ችግር የሚኖረው ግን የወያኔ የሰላማዊ ትግል ትርጉም (definition) ትክክል እንዳልሆነ ህሊናችን እያወቀ ወያኔ ያልፈቀደውን ሁሉ "ውግዝ ከመአርዮስ" ስንልና የወያኔ ግፍና ጭቆና አንገፍግፏቸው ተገደው ብረት ያነሱትን ሁሉ አንዳንድ አዛውንቶች እንደሚሉት "ያልሰለጠናችሁ" ለማለት የዳዳን ጊዜ ነው።

ወያኔን ለመታገልና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ወያኔ በፈቀደው ቀዳዳ ውስጥ ለመጫወት ፈቅደው "የወሰደውን ጊዜ ይፍጅ እንጂ በምናደርገው ትግል ዛሬ በወያኔ እብሪት የተከለከሉት ሰላማዊ ድርጊቶች በትክክለኛ ስማቸው የሚጠሩበት ዘመን ይመጣል" ብለው ከሚጓዙት ጋር መንገዳቸው እንዲቃናላቸውና በእግራቸው እስኪቆሙ ድረስ መርዳት ወያኔን ለመታገል ሁሉን አቀፍ ትግልና ትብብር መደረግ አለበት ብሎ እንደሚያምን ሰው በአንድነት ምስረታ ሂደት ውስጥ የአቅሜን ሁሉ አበርክቻለሁ። እንዲያውም

አብሬያቸው በቆየሁባቸው ጊዜያት  ድርጅቱን ወያኔ በጥርጣሬ እንዲያየው እንዳላደርግ በንግግርም በድርጊትም ከእነርሱ የተለየ አመለካከት እንዳላራምድ በጣም ትልቅ ጥንቃቄ አድርጌያለሁ። ለዚህም እነርሱም ሆኑ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ። ምንም እንኳ እነርሱ ከያዙት የተለየ አቋም ቢኖረኝም ከዚህ በኋላም በትግላቸው እንዲቀናቸው የሚቻለኝን ሁሉ የማደርግ ካልሆነ በቀር እንዳይሳካላቸው የሚፈልግ ልብ የለኝም። እንዲያውም ወያኔን በምርጫ ማሸነፍ ችለው ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ተደርጎ እኔና ወዳጆቼ የተሳሳትን ሆነን ብንገኝ ደስ የሚለኝ እንጂ የሚከፋኝ አይደለሁም። ይልቅስ የሚያንገበግበኝ እነዚያ ጀግኖቼ በሆቴል ቀርቶ በቢሯቸው እንኳ ለመሰብሰብ የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ከሆኑት ከአቶ መለስ ዜናዊ ዘንድ በአማላጅነት ለመላክ ፕ/ር ኤፍሬምን ደጅ ሲጠኑ እንደፖለቲካ ፓርቲ መመዝገብ ህገ መንግስታዊ መብት መሆኑ ቀርቶ ለመመዝገብ እንቅፋት እንዳይሆንባቸው በሚል ስጋት በህዝብ ዘንድ ትልቅ መታመንን የሰጣቸውን ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ መሰረታዊ የሆኑ ተቋማትን ምስረታ ጥያቄዎች በስህተት እንኳ የማያነሱአቸው ሲሆኑ ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ ባይሆንም በምርጫው እንሳተፋለን እንዲሉ ሲገደዱ የፖለቲካው ሜዳ ምን ያህል እንደተዘጋ አፍ አውጥተው መናገር ቢሳናቸው እንጂ በድርጊት ትልቅ መልዕክት እያስተላለፉ ነው ብዬ ስለማምን በእነርሱ ላይ አፌን

አላላቅቅም። ለእነርሱ ያለኝ ክብር መቼም አይቀንስም። ስለእኔ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ይህን ያህል ካልኩ አሁን አገራችን ውስጥ ስላለው ነባራዊ ሁኔታ ትንሽ ለማለት እሞክራለሁ።

## የፖለቲከው ሁኔታ

በወያኔ ህገ መንግስት አንቀጽ 31 ላይ የዜጎች የመደራጀት መብት እውቅና ተሰጥቶታል። ስለዚህ ማንኛውም መደራጀት የሚፈልግ ዜጋ ለወንጀል ካልሆነ በስተቀር መደራጀት መብቱ ነው። ስለዚህ ይህን መብት ለማደናቀፍ መሞከር ወይም እንቅስቃሴውን መግታት ህገ መንግሰቱን መጣስ ስለሚሆን ወንጀል ነው። አሁን ግን በኢትዮጵያችን ወንጀል የሆነው ህገ መንግስቱን መጣስ ሳይሆን ለመደራጀት መሞከሩ ነው።

የቀድሞ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ተቀዳሚ ም/ሊቀ መንበር የሆኑት ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ከጥቂት ወራት በፊት ከሎሎች የፓርቲው አመራር አባላት ጋር ሆነው የፓርቲውን አባላት ለማነጋገር ወደ ደቡብ ክልል ባቀኑበት ወቅት በጉራጌ ዞን በቡታጅራ ከተማ ቆይታ አድርገው አንዳንድ የፓርቲ አባላትን አነጋግረው ሲያልፉ ከክብርት ሊቀመንበሯ ጋር የተወያዩትን አባላት ፓሊሶችና የደህንነት

ሰዎች መጥተው አንዳንዶቹን እስር ቤት አጉረው ሎሎቹን ደግሞ በመኪና ጭነዋቸው ከከተማ አርባ ኪሎ ሜትር ላይ ወደሚገኝ አንድ ጫካ ወስደው በሀይል ከደበደቧቸው በኋላ ልብሳቸውንና ጫማቸውን አስወልቀው ጥለዋቸው ሄዱ።

በዚያን ወቅት ክብርት ሊቀ መንበሯ በሄዱበት ቦታ ሁሉ ያገኙአቸው ህዝብን በማደራጀት በየአካባቢያቸው የሚታወቁ ጠንካራ አባሎቻችን ብዙ አይነት ፍዳ ተቀብለዋል። ዛሬም እንኳን በአንድነት ምስረታ ሂደት ፊርማ ለማሰባሰብ በመሞከራቸው ብቻ ለእስር ስለሚፈለጉ ከመኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለው የሚኖሩ በርካታ አባላትን አውቃለሁ። ለአብነት ያህል ደሳለኝን ከዱራሜ መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ሰዎች ወንጀላቸው የህግ ዋስትና አለን ብለው ለመደራጀት መሞከራቸው ነው። ሌላም ልጨምር። በእስር ቤት በነበርኩበት ጊዜ ያየሁት ነገር ነው። አንድ መንግስቱ የሚባል የአስራ አራት ዓመት ልጅ ከሌሎች ሃያ ገደማ ከሚሆኑ በእድሜ ከእርሱ ከሚበልጡ ልጆች ጋር ታስሯል፡፡ መንግስቱ ከጀልዱ ከአንድ ትምህርት ቤት አብሮት ከታሰረው ከደዊት ኡርጌሳ በስተቀር ሌሎቹን ከዚህ በፊት አይቶአቸው አያውቅም። ምክንያቱም አንዳንዶቹ ከጭሮ፤ አንዳንዶቹ ከደራ፤ አንዳንዶቹ ከኢሉአባቦራ፤ ሌሎቹ ከአርሲ ቦቆጂ አካባቢ የታሰሩ ናቸው። መንግስቱ በኦሮሞ ነጻነት ግንባር

አባልነትና ከሌሎች ግብረአበሮቹ ጋር በመሆን በወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 240/41 የተደነገገውን በመተላለፍ ፌዴሬሽንን ለመገንጠል በመሞከር ወንጀል ተከሶ ፍርድ ቤት ይመላለሳል። በዚህ ልጅ ላይ ለማስረጃ የቀረበበት የሰው ምስክር ነው። ምስክሩ ሲመሰክር መንግስቱን እንደሚያውቀውና አንድ ቀን ከወረዳ ምክር ቤት የመጡ አባላት "ዴሞክራሲና ዴሞክራሲያዊ አንድነት" በሚል ርዕስ ተማሪዎችን ከየክፍሉ እያስወጡ ሲያወያዩ "እኛ የመጣነው ለመማር ነው እባካችሁ እንማርበት ተውን" ብሎ ሲረብሽ ሰምቻለሁ ብሎ መሰከረበት። ይህን የሰሙ የወያኔ ፈራጆች "ከሌሎች ተማሪዎች ተለይተህ እንማርበት በማለትህ የቀረበብህን ክስ ተከላከል ብለንሃል" አሉት።

ዘላለም በዳኜም ከደራ ታሰሮ ከቃሊቲ ፍርድ ቤት ሲመላለስ ወያኔ በፍርድ ወንበር ላይ ያሰቀመጣቸው ጀሌዎች የቀረበበትን ፌዴሬሽንን የመገንጠል ወንጀል እንዲካለከል የበየኑበት "የህገ መንግስቱ አንቀጽ 39 ተግባራዊ ይሁንልን" ማለትህን የአቃቤ ምስክር ያስረዳ በመሆኑ ተብሎ ነው።

ክቡራትና ክቡራን ተማሪው የናንተን ተረት ተረት ልሰማ ሳይሆን የመጣሁት ትምህርት ለመማር ስለሆነ ልማርበት ተውኝ ብሎ መናገሩ ካሳሰረው፡ አንድ ዜጋ ህገ መንግስቱ ላይ

የተጻፈው ተግባራዊ ይሁንልን ብሎ ስለጠየቀ ብቻ በእስር የሚማቅቅ ከሆነ፤ሌላው ለመደራጀት በመሞከሩ ያለ ርህራሄ ከተደበደበ፤ ከታሰረና ከተፈናቀለ እንዲህ ዓይነት ግፍ ሊቆም ይገባል ብለው የሚያስቡ ዜጎች እንዲህ ዓይነቱን እብሪትና ጥጋብ ለማስቆም ምን ማድረግ አለባቸው? የትግላቸውስ ሰላማዊነትና ሰላማዊ አለመሆን በማን ነው የሚወሰነው? በራሳቸው ህሊና ወይስ እብሪት በወጠረው ጉልበተኛ? ህሊና ላለው ፍርዱ ከባድ አይመስለኝም።

የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን የህግ የበላይነት በሌለበትና ሰዎች ህግ በሆኑበት ሀገር፤ለመሰብሰብና ጠቅላላ ጉባኤ ለማካሄድ የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ወደ ሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ በአማላጅነት ለመስደድ፤ የፕ/ር ኤፍሬምን ደጅ መጥናት ሲያስፈልግ ሜዳው በሌለበት በፈለጋችሁት ቡድን ተደራጅታችሁ፤አስቀድማችሁ ደግሞ የተጫዋቾቻችሁን ስም ዝርዝር አጫዋችም ተጫዋችም ለሆነው ምርጫ ቦርድ ልካችሁ ለጨዋታ እንድትመጡ ተጋብዛችኋል ሲባል አባላት ተለይተው ታውቀው ለጥቃት እንዲጋለጡ ለማድረግ ካልሆነ በቀር ምን ሊሆን ይችላል? ፍርዱን ለህሊናችሁ እተዋለሁ።

ከግንቦት 97 ምርጫ በኋላ ወያኔ ትልቅ ትምህርት ቀስሟል። ተቃዋሚዎቹ እንደ ግለሰብም እንደ ተቋምም ተለይተው

ታውቀዋል። አሁን ወያኔ እነዚህን ድርጅቶች ማዳከም አልያም ማጥፋት ሥራዬ ብሎ ተያይዞታል። ህዝቡን ሊያነቁ መብቱን ሊያሳውቁና ሊያነሳሱብኝ የሚችሉት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ሲቪክ ማህበራት እና ነጻው ፕሬስ ናቸው ብሎ ደምድሟል። እያንዳንዳቸውን ለማሽመድመድ አሊያም ለማጥፋት የሚቻልባቸውን ህግጋት እያረቀቀ ነው። ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ህጋዊ ሽፋን መስጠት ያስፈለገው ለነጭ ወዳጆቹ ሲባል እንጂ ወያኔ በእርግጥ እነዚህን ተቋማት ለማጥፋት ህግ አያስፈልገውም። በቂ ጉልበት አለኝ ምንም አታመጡም ብሎአል።

ህጉ ሲረቀቅ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተሳትፈዋል አስተያየታቸውንም ሰጥተዋል የሚል የተለመደውን የፖለቲካ ትርፍ ከወዳጆቹ ያስገኝልኛል በሚል ስሌት መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት ትምህርት ለመስጠት ባዘጋጁት መድረክ ላይ በስልጣናቸው የሚመጣባቸው ሁሉ የሳቸውም ለአምሳና ከዚያ በላይ ዓመታት መግዛት ለሚፈልገው ድርጅታቸው ጠላት እንደሆነ ሲያስረዱ አቶ መለስ “በቢላዋ ቀልድ የለም ብላለች ዶሮ” “ድርጅታችንም ተገትሮ መሰበር ስለማይፈልግ እንዲህ አይነቱን ስለመብት ህዝቡን አስተምራለሁ የሚለውን ድርጅት ሊያየው አይፈልግም” ብለው በማያሻማ ሁኔታ ግልጽ አድርገዋል።

ከውይይቱ በኋላ ካነጋገርኳቸው በውይይቱ ከተሳተፉ አንዳንድ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች መሪዎች መካከል አንዱ በጣም መረር ብሎ "ከዚህ በኋላ አማራጮች ሁሉ ተዘግተው አንድ በር ብቻ ነው ወለል ብሎ ተከፍቷል። እርሱም የሀይል በር ነው" አለኝ። እናንተስ ምን ትላላችሁ?

## ኢኮኖሚያዊ ገድታ

የኢኮኖሚውን ሁኔታ በሚመለከት በአንድ ወገን ባለፊት አራት አመታት ተከታታይ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገባቸውንና ይህም በውጭ ድርጅቶች በተለይም በአይ፡ኤም፡ኤፍ እና በአለም ባንክ መመስከሩን የወያኔ መገናኛ ብዙሃን ቀንና ማታ እየተናገሩ ይውላሉ ያመሻሉ። በተጨማሪም ተገኘ የተባለው እድገት እውነት መሆኑን በአንደበታቸው የሚመሰክሩ ግን ገጽታቸው ጉስቁልናቸውን እንጂ ብልጥግናቸውን የማያሳዩ የገበሬ ሚሊዬነሮችን በቴሌቪዥን መስኮት ማቅረብ የዕለት ተለት ሥራቸው አደረጉት።

ውሎ ሲያድር ከእድገቱ የከተሜው ደሃ አለመቋደሱን አምነው ለኑሮ ውድነት ጦስ የዳረጉን ግን ቻይና ህንድና የነዳጅ ዋጋ በአለም አቀፍ ገቢያ መናር ናቸው አሉን። ለዚህም አንዳንድ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ይደረጋል ገበያውም ይረጋጋል አሉን።

ከማሻሻያው በኋላም የኑሮ ውድነቱ እየቀለለ እየሄደ እንደሆነ ከኑሮ ውድነት መቅለል የተጠቀሙ አንዳንድ የአዲስ አበባና የክልል ከተሞች ነዋሪዎች እንደገለጹት እየተባለ መስማት ቀጠልን። ያም ሆኖ ግን የገጠሩ ህዝባችን ባለፉት አራት አመታት ከተገኘው የኢኮኖሚ እድገት ተቋዳሽ ነው በሚሉት ሽንገላ የገጠርን የምቾት ኑሮ ሊያስመኙን ብዙ ደከሙ። እነ አይ፡ኤም፡ ኤፍም ይህን መስክረዋል ሲሉ ሰነበቱ።

ታዲያ በዚህ ጊዜ ረሃብ ውስጥ ውስጡን በተለይም የገጠሩን ህዝብ ይገዘግዘው ኖሮ በምቾቱ የከተማው ሕዝብ እንዲቀናበት የነገሩን ያ ምስኪን የገጠር አፈር ገፊ በሚሊዮኖች በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ እንደሆነ ከእርዳታ ድርጅቶች መስማት የጀመርነው። አሁን ጸቡ በረሃብተኛው ቁጥር ላይ ሆኗል፡፡ በአንድ ወገን ምግብ ፍለጋ ወደ እርዳታ ሰጭች የሚጎርፈው ህዝብ ቁጥር እየጨመረ በሌላ ወገን ደግሞ ተርቦም ለመራቡ ከወያኔ ሰርቲፊኬት ማግኘት ብርቅ ሆነበት በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ የአቶ መለስ አንጀት እስኪራራ ድረስ የመናገር የመደራጀት የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ የፈለገውን የፖለቲካ ድርጅት የመደገፍ መብት እንዳጣ ለመራብም የመንግስት ፈቃድና እውቅና የሚያስፈልግ ሀገር ሆኖበት የሰው ልጅ በመሆን ውስጥ ያለን ክብር ለአፍታም ሳያይ ለዘላለሙ እያሸለበ ነው።

የህግ የበላይነት ባልሰፈነበት ዴሞክራሲዊ ስርዓት ባልተመሰረተበት ህገ አራዊት በነገሰበት ሁሉ ህይወት እንዲህ ነች። ከዚህ ለመገላገል ምንም ዓይነት እርምጃ መውሰድ በእኔ ብቻ ሳይሆን በማናችሁም ህሊና ትክክል ሊሆን ይገባል ብዬ አምናለሁ።

ህዝቡ ከግንቦት ምርጫ በኋላ ወያኔ በወሰደው መጠነ ሰፊና አሰቃቂ የሀይል እርምጃ ከፖለቲካ ፓርቲዎች በተለይም በቅንጅት መከፋፈል ከደረሰበት የሞራልና የስነልቦና ቀውስ ሳያገግም በኑሮ ውድነት ስቃይ እና በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ ይገኛል። በእነዚህና ባለፉት በርካታ አመታት በሀገራችን ህዝብ ላይ የተነሱት አገዛዞች ያደረሱበት በደል ተዳምሮ ሊፈነዳ ያለ ከፍተኛ የሆነ የታመቀ ምሬት በህዝቡ ውስጥ መስፈኑ በእጅጉ ይስተዋላል። በአንድነት ፓርቲ ምስረታ ወቅት ፊርማ ለማሰባሰብ ወደ ተለያዩ ክልሎች በተሰማራንበት ጊዜ እኔም ሆንኩ ሌሎቹ ሰዎች ካነጋገርናቸው ሰዎች የታዘብነው ነገር ቢኖር በህይወት ተስፋ የመቁረጥና የምሬት መንፈስን በህዝቡ ውስጥ በሀይል መስፈኑን ነው። ይህን በህዝቡ ውስጥ የተከማቸውን ምሬት የሚጠግን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታ በአፋጣኝ የማይፈጠር ከሆነና በጊዜ ሂደት በራሱ የፈነዳ ዕለት ከማናችንም አእምሮ የማይጠፋ ጸጸት ጥሎ የሚያልፍ ሁኔታ

ሊመጣ እንደሚችል በዚህ አጋጣሚ ሳላስገነዝብ ማለፍ አልፈልግም።

## ምን እናድርግ?

የኢትዮጵያችን ችግር ለከት የለውም። እያደር እየተወሳሰቡ የሚሄዱ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮች አሉብን። ይህ መንግስት ስራዬ ብሎ ላለፉት 17 አመታት እርስ በእርሳችን ሲያባላን፤ በውስጣችን ከፍተኛ ጥርጣሬ እንዲፈጠርና እንዳንተማመን፤ አንድ ከሚያደርጉን ነገሮች ይልቅ የሚለያዩን ነገሮች የሚገዝፉ መስሎን እንዳንተባበርና በጋራ እንዳንታገል የእለት ተእለት ፕሮጀክት አድርጎት ብዙ ሚሊዮን ብር እያወጣ ይሰራል። ይህን እሱ ማድረጉ ሊገርመን አይገባም። የሚገርመው ግን ይህን ተረድተን ለመተባበር ካልቻልን ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ከፊታችን የገጠመን ችግርና ከዚህ ችግር ለመውጣት የሚያስፈልገንን የመፍትሄ ሀሳብ ለመረዳት በፍጹም ሊከብደን አይገባም። ጥያቄው ምን አይነት መንግስት ይኑረን የሚለው ነው። ሊኖረን የሚገባው መንግስት ደግሞ በሕዝብ የተመረጠ መንግስት ብቻ መሆን እንዳለበት ብዙ የሚያከራክር ሊሆን አይገባም። ስልጣን ላይ የሚወጣው ማን ይሁን? የሚለውን ሕዝቡ ይወስን በሚለው ላይ ጸብ ከሌለ ያሉንን የፖለቲካ ልዩነቶች በኋላ ለህዝቡ አቅርበን

ህዝቡ የሚወስነውን ለመቀበል ከተስማማን፤ ይህን የጨዋታ ህግ ተግባራዊ ለማድረግ ተባብረን ለመታገልና ይህንን አድል ነፍጎ እያዋረደ ሊገዛን የቆረጠን የጥቂት ወሮበሎች መንግስት ማስወገድ እንዴት ያቅተናል? የግንቦት ሰባት ጥሪ ይህ ነው። ቀላል ነው። ለማንም ሊገባ የሚችልና ያልተወሳሰበ ነው። ጊዜው ከዳር ሆነን የምናይበት አይደለም። ጉዳዩ ጊዜ የሚሰጥ ስላይደለ። በጊዜ ካልደረስንለት በኋላ የምንጣላበት አገር አንኳን ላይኖረን ይችላል። ስለዚህ እንተባበር አገራችንንም ሊመጣ ካለው አደጋ እንታደጋት።

አገራችንን እግዚአብሄር ይባርክ!!

አመሰግናለሁ።

አመሰግናለሁ።